- ተመላሽ ዜጎች ኦርጅናል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማረጋገጫ ያረፈበት የኢምባሲው ወይም የቆንስላ ጀኔራል ጽ/ቤት ደብዳቤ፣ ፓስፖርት፣ ሊሴ ፓሴ፣ የማስጫኛ ሰነዶች፣ የዕቃ ዝርዝር መግለጫ እና ሌሎች ማስረጃቸውን በመመሪያ ቁጥር 51/2010 አንቀጽ 6 መሰረት በጥንቃቄ እንዲይዙ፤ ከጠፋ መስተናገድ እንደማይችሉ ማስገንዘብ

- ከአንዳንድ ሚሲዮኖች የቀረጥ ነጻ ድጋፍ በሚጻፍበት ጊዜ መካተት ያለባቸው ነገሮች ሳይካተቱ በመቅረታቸው ተመላሽ ዜጎች እቃዎቻቸውን ለማውጣት መጉላላት እየደረሰባቸው በመሆኑ ወደ ጽ/ቤታችን በመምጣት የድጋፍ ደብዳቤ እንዲፃፍላቸው የሚጠይቁ ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ የድጋፍ ደብዳቤ ለመስጠት የሚያስችሉን መነሻ መረጃዎች በለሌሉን ዜጎች እየተቸገሩ ይገኛሉ።

በመሆኑም ዜጎቻችን ወደ አገር ቤት ከገቡ በኋላ የሚያጋጥማቸውን እንግልትና ያልአስፈላጊ ኪሳራ ለማዳን ሚሲዮኖቻችን ከተለመደው አሰራር ወጣ በማለት የአሰራር ዘዴዎችን በመቀየስ መመሪያውን ለዜጎች (በኮሚኒቲ ማህበራት፣ በእድሮች፣ በእምነት ተቋማት፣ ሬስቶራንቶች ወዘተ (በማሰራጨት) ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር 51/2010 አንቀፅ 9(1) በተመለከቱት የግል መገልገያ ዕቃዎች መመሪያ በውል መረዳት እንዲችሉ ሚሲዮኖቻችን ተደራሽ ለማድረግ ከሚያከናውኑት ተግባር በተጨማሪ በዌብሳት፣ በሶሻል ሚዲያ እና የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለባለመብት ዜጎች ግንዛቤ በመፍጠር የዜጎችን ቅሬታ መቅረፍ እንዲቻል መመሪያውን ከዚህ ጋር በማያያዝ በድጋሚ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

መስፍን ገብረማርያም ሽዎ
የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክተር
ጀኔራል

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Foreign Affairs

አባሪዎች፦ የግል መገልገያ ዕቃዎች መመሪያ ቁጥር 51/2010

- መመሪያ ቁጥር 51/2010 አንቀፅ 9(1) የተሰጠ ማብራሪያ

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለክቡር ሚኒስትሩ ካቢኔ ጽ/ቤት
- ለሁሉም ሚኒስትር ዲኤታ ጽ/ቤቶች

**ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**<u>አዲስ አበባ</u>**